11ኛ ዓመት ቁጥር 25
11$^{th}$ Year N$^{o}$ 25

ባህር ዳር ሐምሌ 14 ቀን 1998 ዓ.ም
Bahir Dar 21$^{st}$ July, 2006

# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት

# ዝክረ-ሕግ

# ZIKRE HIG

## OF THE COUNCIL OF THE AMHARA NATIONAL REGIONAL STATE IN THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA



| | | | |
|---|---|---|---|
| የአንዱ ዋጋ ብር 8.20 Price | በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ | ISSUED UNDER THE AUSPICES OF THE COUNCIL OF THE AMHARA NATIONAL REGIONAL STATE | የፖ.ሣ.ቁ P.o. Box 312 |



| ማውጫ | CONTENTS |
|---|---|
| ደንብ ቁጥር 40/1998 ዓ.ም | Regulation No. 40/2006 |
| በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የደሴ ንግድና ሥራ አመራር ኮሌጅ ማቋቋሚያ ደንብ ማሻሻያ ክልል መስተዳድር ምክር ቤት ደንብ | The Amhara National Regional State Dessie Business and Management College Establishment, Council of Regional Government Amendment Regulation. |

## ደንብ ቁጥር 40/1998 ዓ.ም

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የደሴ ንግድና ሥራ አመራር ኮሌጅ ማቋቋሚያ ደንብን ለማሻሻል የወጣ ክልል መስተዳድር ምክር ቤት ደንብ

## REGULATION NO.40/2006

A COUNCIL OF REGIONAL GOVERNMENT REGULATION ISSUED TO PROVIDE FOR THE AMENDMENT OF THE DESSIE BUSINESS AND MANAGEMENT COLLEGE ESTABLISHMENT REGULATION OF THE AMHARA NATIONAL REGIONAL STATE.

ከታሪክ በመነጨ ምክንያትና የአካባቢውን ሕብረተሰብ ፍላጐት መሠረት በማድረግ የደሴ ንግድና ሥራ አመራር ኮሌጅን ስያሜ መለወጥና በአዲስ መተካት በማስፈለጉ፤

WHEREAS, it has been found appropriate to alter or substitute the designation of Dessie Business and Management College due to historical grounds as well as on the basis of the interest of the surrounding community thereof;

ይህንኑ መፈፀም የሚቻለው ደግሞ ኮሌጁ የተቋቋመበትን ደንብ በማሻሻል ብቻ ሆኖ በመገኘቱ፤

WHEREAS, such is in fact accomplished by solely amending the regulation which has established the college;

የአማራ ክልል መስተዳድር ምክር ቤት በተሻሻለው የብሔራዊ ክልሉ ህገ-መንግስት አንቀፅ 58 ንዑስ አንቀጽ 7 እና የክልሉን ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ማስፋፊያ ኤጀንሲ ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 87/1995 (እንደተሻሻለ) አንቀፅ 15 ድንጋጌዎች በተሰጠው ስልጣን መሠረት ይህንን ደንብ አውጥቷል።

NOW, THEREFORE, the Council of the Amhara National Regional Government, in accordance with the powers vested in it under the provisions of Art. 58 Sub. Art. 7 of the revised Regional Constitution and Art.15 of the Regional Technical and Vocational Education and Training Agency Establishment Proclamation No. 87/2003, (as amended), hereby issues this regulation as follows.

## 1. አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ "የደሴ ንግድና ሥራ አመራር ኮሌጅ ማቋቋሚያ ደንብ ማሻሻያ ክልል መስተዳድር ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 40/1998 ዓ.ም" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

## 1. Short Title

This regulation may be cited as the "The Dessie Business and Management College Establishment, Council of the Regional Government Amendment Regulation No. 40/2006."

## 2. ማሻሻያ

የደሴ ንግድና ሥራ አመራር ኮሌጅ የተቋቋመበት የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 12/1995 ዓ.ም በዚህ ደንብ ተሻሽሏል፦

ሀ. የደሴ ንግድና ሥራ አመራር ኮሌጅ ይህ ደንብ ከሚፀናበት ቀን ጀምሮ የወ/ሮ ስህን ንግድና ሥራ አመራር ኮሌጅ በመባል የሚጠራ ይሆናል።

## 2. Amendment

The Dessie Business and Management College Establishment Council of the Regional Government Regulation No. 12/2003 is hereby amended as follows:

a. The Dessie Business and Management College shall be renamed as Wizero Sihin Business and Management College as of the day, on which this regulation comes into force.

ለ. በቀዳሚው ደንብ ውስጥ ነባሩን ስያሜ የሚጠቅሱ ድንጋጌዎች ሁሉ በዚህ ደንብ መሠረት አዲሱን የኮሌጁን ስያሜ እንደጠቀሱ ሆነው ይቆጠራሉ።

b. All provisions in the former regulation citing the previous designation of the college shall be presumed to have been mentioning the new name of the college pursuant to this regulation.

3. **ደንቡ ስለሚፀናበት ጊዜ**

ይህ ደንብ በክልሉ መንግስት ዝክረ-ህግ ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

3. **Effective Date**

This regulation shall came into force as of the date of its publication in the Zikre Hig Gazette of the Regional State.

ባህር ዳር
ሐምሌ 14 ቀን 1998 ዓ.ም
አያሌው ጎበዜ
የአማራ ብሔራዊ ክልል
ርዕሰ መስተዳድር

Done at Bahir Dar
This 21st day of July, 2006
Ayalew Gobezie
Head of Government of the
Amhara National Regional State